የሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 17 እና 18

1. ዐሥሩ ለምጻሞች ምሳሌነታቸው ምንድነው?
ሀ) የ ዐሠርቱ ትዕዛዛት
ለ) 9ኙ የክፉ ኅሊናት 1ዱ የበጎ ኅሊና
ሐ) 9ኙ የ9ኙ ቅዱሳን 1ዱ የሰይጣን
መ) ሁሉምመልስ ናቸው

2. ፈሪሳውያን ስለእግዚአብሔር መንግሥት በጠየቁ ጊዜ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምን ብሎ መለሰ?
ሀ) በመካከላቸው እንደሆነች ተናገረ
ለ) በምድረ በዳ ወጥተው አጥብቀው ቢፈልጓት እንደሚያገኟት ነገራቸው
ሐ) ለአይሁድ ብቻ የተሰራች ስለሆነች ከነርሱ ውጪ የሚያያት እንደሌለ ነገራቸው

መ) ሳይታክቱ እንዲጠብቋት ነገራቸው

3. በምዕራፍ 17 ላይ የሎጥ ሚስትን አብነት አድርጉ የተባለው ስለምን ነው?
ሀ) በሰዶም እጅግ የከፋ በደልን ሲፈጽሙ እርሷም አብራ ኃጢአትን ሰርታ በእሳት ስለተቃጠለች
ለ) መልአክ ከሰዶም ሲያወጣቸው ወደኋላ እንዳትዞሩ ቢላቸውም ድምጽ ሰምታ በመዞሯ የጨው ሐውልት ሆና ስለቀረች
ሐ) የሰዶም ከተማ በእሳት ስትጠፋ ልጆቿ እንዳይቃጠሉባት ደብቃ ስላስመለጠቻቸው
መ) ለሰዶም ሰዎች ምሕረቱን እንዲያወርድና በእሳት እንዳይጠፉ ወደ እግዚአብሔር ስለለመነች

4. መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወንድማችን ቢበድለን ምን እንድናደርግ መከረን?
ሀ) በህግ እንድንጠይቀው ለ) ለወላጆቻችን እንድንናገር ሐ) ለብቻው እንድንመክረው መ) ከልባችን እንድንቀየመው

5. ጌታችን ከእነዚህ ከታናናሾቹ አንዱን የሚያሰናክል አህያ የሚፈጭበት ወፍጮ በአንገቱ ታስሮ ወደ ጥልቁ

ባሕር ቢሰጥም ይሻለዋል ስላለበት ምክንያት ልክ ያልሆነው የቱ ነው?
ሀ) አንድ ክርስቲያን በጉዞው ሁሉ ለሌሎች በጎ ምሳሌ እንጂ ማሰናከያ መሆን እንደሌለበት ሲናገር ነው
ለ) የሃይማኖት መሪዎች ለምእመናን በጎ ምሳሌ መሆን አለባቸው ሲል ነው
ሐ) ወልድ ዋህድ ብለው ካመኑ ምእመናን አንዱን ያሰናከለ ሰው ራሱን ማጥፋት እንደሚገባው ሲናገር ነው
መ) ከምእመናን መካከል አንዱን ያሳተውን ሰው ጽኑ ቀኖና ሰጥተው ባሕር በተባለው የንስሐ እንባ ቢያሰጥሙት ይሻለዋል

6. "ሁለት ሰዎች በእርሻ ይኖራሉ፤ አንዱን ይወስዳሉ ሁለተኛውንም ይተዋሉ... " የሚለው ክፍል የሚያሳየው
ሀ) መንግሥተ ሰማያት በእጣ እንደሚገባ
ለ) በምግባር በሃይማኖት የጸናውን ወደ መንግሥተ ሰማያት እንደሚያገቡት፣ ያልጸናውን ወደ ገሃነም እንደሚጥሉት
ሐ) ከሁለት ሰዎች አንዱ ብቻ ሊድን እንደሚችል
መ) ሁሉም

7. የሉቃስ ወንጌል 18፥16 ላይ ጌታችን “ሕፃናትን ተዉአቸው፥ ወደ እኔም ይመጡ ዘንድ አትከልክሉአቸው፤ የእግዚአብሔር መንግሥት እንደነዚህ ላሉ ናትና” ሲል ምን ለማለት ነው?
ሀ) ቂም በቀል የማያውቁ
ለ) ፍፁም ፍቅርን የተላበሱ
ሐ) ጨዋታን የሚያበዙ
መ)ሀ እና ለ

8. በሉቃስ ምዕራፍ 18 ላይ ያለው ባለፀጋ ለምን አዝኖ ተመለሰ?
ሀ) ምንም ንብረት ስለሌለው
ለ) ብዙ ንብረት ስለነበረው
ሐ)ብዙ ግመሎች ስለነበሩት
መ) ሁሉም

9. ጌታችን "የሰው ልጅ" ብሎ በእርሱ ላይ ስለሚደርሱት መከራዎች ከጠቀሳቸው ውስጥ የማይካተተው የቱ ነው?
ሀ) ለአሕዛብ አሳልፈው ይሰጡታል

ለ) ይገድሉታል
ሐ) ቀይ ግምጃ ያለብሱታል
መ) ይተፉበታል
ሠ) መልስ የለም

10. "መከራን ከራሱ ለሚያመጣት ወዮለት" የተባለው ስለ ማን ነው?
ሀ) ጴጥሮስ ለ) ይሁዳ ሐ) ዮሐንስ መ) መልሱ የለም

11. ከዐሥሩ ከለምጽ የዳኑ ሰዎች ከዳነ በኋላ ወደ ጌታ ሄዶ በግንባሩ ተደፍቶ የሰገደው ትውልዱ ምንድን ነው?
ሀ) ሳምራዊ ለ) ከነናዊ ሐ) ፈሪሳዊ
መ) ሶርያዊ

12. "የእግዚአብሔር መንግሥት እነሆ በመካከላችሁ ነች" ሲል ምን ለማለት ነው?
ሀ) መንግሥተ ሰማያት በምድር ላይ ነች ለማለት ነው
ለ) መንግሥተ ሰማያት እኔን ማመን ነው ሲል ነው
ሐ) ዳግም ምጽዐት የለም ሲል ነው
መ) መልሱ የለም

13. በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 17 ላይ ከሎጥ ሚስት ታሪክ የምንማረው ምንድን ነው?
ሀ) መላእክትን አለመታዘዝ
ለ) ጓደኞቻችን ሲጎዱ መርዳት፣ ማዘን እንደማይገባ
ሐ) ከመነኑ በኋላ ወደ ዓለም መመለስ ከንቱ እንደሚያደርግ
መ) ለ እና ሐ

14. በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 18 ላይ ለድሃዋ ሴት እንዳትዘበዝበው ብሎ ከፈረደላት መኮንን ታሪክ ምን እንማራለን?
ሀ) ለጓደኞቻችን እንዳይጨቀጨቁን ብለን የማይገባም ነገር ቢሆን ማድረግ እንዲገባ
ለ) ሰዎች እስኪለምኑን እና እስኪጨቀጨቁን ድረስ በጎ ማድረግ እንደማይገባ
ሐ) ጸሎትን ደጋግሞ መጸለይ እንጂ ተስፋ ቆርጦ መተው እንደማይገባ
መ) ሁሉም

15. በፈሪሳዊው እና በቀራጩ ታሪክ ላይ ቀራጩ

በእግዚአብሔር ዘንድ ከብሮ ተመለሰ የተባለው ለምንድነው?
ሀ)ኃጢአቱ ስለበዛ
ለ)በትሕትና ራሱን ዝቅ ስላደረገ
ሐ)ዐሥራት ከማውጣት ይልቅ ኃጢአት ዋጋ ስላለው
መ)ሀ እና ሐ

16. በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 18 ላይ ሐዋርያት ሕፃናትን ያመጧቸውን ሰዎች የገሰጹት ለምንድነው?
ሀ)በዚያ ራሳቸውን ለእግዚአብሔር ጃንደረባ ያደረጉ (በድንግልና የሚኖሩ) ስለነበሩ
ለ)ሐዋርያት ወንጌል ለሕፃናት መሰበክ የለበትም ብለው ስላሰቡ
ሐ)የትምህርት ጊዜያቸውን እንዳይሻሙባቸው
መ)ስልጣናቸውን መጠቀም ስለፈለጉ ብቻ

17. "ሂደህ ያለህን ገንዘብህን ሁሉ ሸጠህ ለድሆች ስጥ፤ _____"
ሀ)መጥተህ ተከተለኝ
ለ)በሰማይ መዝገብ ታገኛለህ
ሐ)በምድር ብዙ ሃብት ታገኛለህ

መ)ሁሉም
ሠ)ሀ እና ለ

18. ግመል በመርፌ ቀዳዳ ያሳለፈው ሐዋርያ ማን ነው?
ሀ) ቶማስ ለ) ታዴዎስ ሐ) ጴጥሮስ መ) ያዕቆብ

19. በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 18 ላይ ጌታ ዕውሩን ያበራው በየት ነበር?
ሀ) በኢያሪኮ ለ) በገሊላ ሐ) በናዝሬት መ) በናይን

20. በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 17 ላይ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ካነፃቸው ለምጻሞች ስንቱ ተመለሱ?
ሀ)1 ለ)2 ሐ)3 መ)10